


## ፈጠነ እሸቱ

የቀይ ሽብር ሰለባ የሆነ (አ.አ)


# ኢትዮጵያ

የካቲት 2005 | 1ኛ ዓመት ቁጥር 8 | በነፃ የሚሠራጭ



ርእሰ አንቀጽ

ገጽ 2

ዜና ከተባለ

ገፅ3

ምን ይሰማ........ ኣገር

ገፅ3

ትላንትና

ማይኔክስ



ገፅ 5

ነፃ ሀሳብ

ያለው አንድ ሲኖዶስ ነው፤ ጳጳሱም አቡነ መርቆሬዎስ ናቸው::

ገፅ 6


## ወያኔ 9 የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትን አሰናበተ፤ ኦህዴድም ሶስት አንጋፋ ባለስልጣናቱ ከስራ አስፈጻሚ አባልነት አባረረ

እሁድ መጋቢት 8 ቀን 2005 ዓ.ም. የወያኔ 11ኛ ጠቅላላ ጉባኤ መቀሌ ከተማ ላይ የተደረገ ሲሆን ከየቦታው በተሰበሰቡ የወያኔ አባላት መሀከል የተፈጠረው ክፍፍል በግልጽ የታየበት አንደኛው ወገን አይሎ የወጣበት መድረክ እንደነበር በስፍራው ከነበሩ ወገኖች የተገኘው ዜና ይጠቁማል;

ጉባኤው ሲደረግ ከነበረበት ጊዜ በወራት ያህል ያራዘመው የወያኔ ቡድን በውስጡ የተፈጠረውን ሽኩቻና የእርስ በእርስ ክፍፍል እልባት ለመስጠት በሚል አራዝሞ የቆየ ሲሆን ሰሞኑን በመቀሌ ባደረገው በዚሁ ጉባኤ ላይ የተባረሩ የቀድሞ አመራሮች ይመለሱ ብለው ይፎከሩ የነበሩት የወያኔ አባሎች በቁጥር ከፉኛ ተበልጠው የታዩበት መድረክ እንደነበርም የደረሰን ጥቆማ አጋልጧል።

በወያኔ አመራር መሀከል ክፍፍል መኖሩን ያመነው የድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የሆነው ብርሃነ ኪዳነማርያም የተባለው ግለሰብ በበኩሉ በህወሃት ውስጥ የተፈጠረው ክፍፍል አዲስ እንዳልሆነና ከጫካ ጀምሮ የመጣ መሆኑ ጠቅሶ አሁንም ይኸው ትግል እብሮ ያለና በቅርቡ የሚቀረፍ እንደሆነ መግለጹ እስከ ዛሬ ሲናፈስ የነበረውን ወሬ እውነት መሆኑን አረጋግጧል። በምስጢር ታፍኖ ለብዙ ጊዜ ተይዞ የነበረው የወያኔ ክፍፍል በ 11ኛው ጉባዔ ላይ ላይ በግልጽ ወጥቶ የመነጋገሪያ ርዕስ ሆኖ የሰነበተ ሲሆን የአባ አባይ ወልዱ ቡድን ግን የበላይነቱን ያስመሰከረበት ነው ተብሏል። ህወሃትን መለሰ ቀብሮት ነው የሄደው ስለዚህ የተወገዱ የህወሃት ባለስልጣናት ወድ ድርጅቱ እንዲመለሱና ትንሳኤውን እንዲያሳዩን በሚል ሰፊ ቅስቀሳ ሲያደርግ የነበረው ስብሃት ነጋ እየተሸነፈ ከመምጣቱ በጤጨማሪ በጉባኤው ላይ ሳይገኝ ቀርቷል። እነ ስብሃት ነጋ የታችኛውን አመራር አባላት በተለያዩ ስልቶች ጠልፈው መያዛቸውን ያረጋገጠው የአባይ ወልዱ ቡድን በበኩሉ የተለያዩ የጦር ክፍል አዛዦችን እየተዘዋወረ በማግባባት ወደራሱ ቡድን የቀላቀላቸው ከመሆኑም በላይ እነስብሃት የህወሃት አፍራሽ አድርጎ በማቅረቡ ሰፊ ድጋፍ ከጦሩ አዛዦች ሊያገኝ እንደቻለም ለማወቅ ተችሏል። የሰሜን አዛዥ የሆነው ሰዓረ መኮንን ከአባይ ወልዱ ጋር በመሆን በእዙ ስር ያሉትን የጦር አዛዥ የሆኑትን የወያኔ አባላት በሙሉ አሳምኖ ለቡድኑ እንዲወግኑ ያደረገ ከመሆኑ ባሻገር የእነ ስብሃት ነጋ ቡድን ህወሓትን አዳክሞ ለሌላ አሳልፎ ሊሰጥ በመሆኑ ለሁላችንም የህልውና ጥያቄ ነው በማለትም ሰፊ ቅስቀሳ ሲያደርግ እንደነበር ታውቋል።

መቀሌ ከተማ ውስጥ በተደረገው 11ኛ ጉባኤ ላይ በቻይና ሀገር በአምባሳደርነት እየሰራ የሚገኘው የቀድሞው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍንም የሽምግልና ስራውን አጠናክሮ በመሄዱ ጉባኤው ያለ ብጥብጥ ሊቋጭ የቻለ ቢሆንም በማእከላዊና በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫ ላይ ከፍተኛ ሙግትና ትግል ገጥሞት እንደነበርም የደረሰን ጥቆማ ገልጽዋል። መለስ የጀመረውን መተካካት የሚለውን ስልት በመጠቀም የእነ አባይ ወልዱ ቡድን ሰሞኑን በተደረገው ጉባዔ ላይ ከእነ ስብሃት ጋር የወገነውንና ከመለስ ጋር ሆድና ጀርባ ሆኖ የቆየውን አርከበ እቁባይንን፤ መሀል ሰፋሪ ሆኖ ግራ ተጋብቶ የቆየውን ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ብርሃነ ገብረክርስቶስ፣ሽምግልና ይዞ ላይ ታች ሲል የነበረውን ስዩም መስፍንን እንዲሁም ጠንካራ ተሚጋች ነው የተባለው ዘርዐይ አስገዶምን ከማዕከላዊ ኮሚቴና ከስራ አስፈጻሚነታቸው ሙሉ ለሙሉ ያባራራቸው ሲሆን መንግስተ አብ ገብረ ኪዳን፣ መሰረት ገብረማርያም ፤ደሴ በዛብህ፣ ይሄይሽ ለማ፣ ንጉሴ ገብሬ የተባሉትን ከማእከላዊ ኮሚቴ ያባረረ መሆኑ ታውቋል።

የወያኔ ጀሌ የሆኑት ሶስቱ ድርጅቶች በበኩላቸው በባህር ዳር በአዋሳና በናዝሬት/አዳማ ከተሞች ጉባኤያቸውን አድርገው የማእከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈጻሚ አባላትን መርጠዋል ኦህዴድ 81 የማእከላዊ ኮሚቴ አባላትና 9 የስራ አስፈጻሚ አባላትን የመረጠ ሲሆን እንደ ወያኔ መተካካት የሚለውን ስልት በመጠቀም ኩማ ደመቅሳን ግርማ ብሩንና አባዱላ ገመዳን ከስራ አስፈጻሚነት ያባረራቸው ሲሆን በምትካቸው ከማዕከላዊ ኮሚቴ አዳዲስ የተባሉ ካድሬዎች ተመርጠው ወደ ስራ አስፈጻሚነት መግባታቸው ታውቋል።

ብአዴንም በበኩሉ 65 የማዕከላዊ ኮሚቴ ና 9 የስራ አስፈጻሚ አባላት የመረጠ ሲሆን በ2003 ዓ.ም. በናዝሬት በተደረገው ጉባኤ ላይ መተካካት ተብሎ በጡረታ የተሰናበተው አዲሱ ለገሰ ተመልሶ የብአዴን የስራ አስፈጻሚ ሆኖ ተመርጧል ተብሏል;፡ ደህዴን 55 የማእከላዊ ኮሚቴና 9 የስራ አስፈጻሚ አባሎችን መርጦ ያቀረበ ሲሆን ነባር የስራ አስፈጻሚ ከነበሩት መካከል ሁለቱን ማለትም ለገሰ ጫፎንና ደበበ አበራን አባርሮ በምትካቸው ደሴ ዳልኬንና ተስፋዬ ባልጅግ የተባሉትን መርጧል።

### ወያኔ ቻይናን ሲያወድስ ምእራባውያንን ሲያብጠለጥል ሰነበተ


ከቻይና ጋር ፍቅር የያዘው ወያኔ ሰሞኑን፣ በሚያሳትመው አዲስ ራዕይ መጽሔት፣ ምዕራባውያንን ሲያብጠለጥል በአንጻሩ ደግሞ ቻይናን ሲያወድስ ሰንብቷል፡፡

ለይስሙላ የወያኔ መሪ ሆኖ የተቀመጠው ሀይለማሪያም ደሳለኝ ሰሞኑን ከቻይና ቴሌቪዥን ጣቢያ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ እየተካሄደ ያለው መሠረተ ግንባታ ቻይና ባትኖር ኖሮ እዚህ ደረጃ አንደርስም ነበር ሲል ደመመጡ ዲፕሎማቶችን ጭምር ሲያነጋግር ሰንብቷል፡፡የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ ዓመት ነው እያሉ የኖሩት የወያኔ መሪዎች አሁንም የሀገሪቱን እና የህዝቧን ታሪክ አሽቀንጥረው በመጣል ቻይና ባትኖር ኖሮ ኢትኦጵያ ከቶ አትኖርም ነበር በማለት እጅግ በሚያሳፍር ሁኔታ መግለጫ መስጠታቸው መላው የሀገሪቱን ህዝብ እና ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆኑ ዲፕሎማቶችን እያነጋገረ እንደሚገኝ ታውቋል፡፡

ወደ 4ኛው ገጽ ዞሯል

## ኢትዮጵያ ጋዜጣን

*በተለያዩ ድረ ገጾች
ሀ. Eprp.com
ለ. Asimba.org
ሐ. Debteraw.com
ወዘተ.
*በ Face book (ethiopianewspaper)




# ኢትዮጵያ

**በኢሕአፓ የዲሲና አካባቢው ደጋፊ አካል**

**የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ**



አድራሻ 5309 Georgia Ave. NW. 2nd fl. Washington DC 20011

ስ/ቁ 202 291 4217

ኢሜል dc.region.eprp@gmail.com


## ርዕሰ አንቀጽ

## ጀግኖቹን የማያከብር ኅብረተሰብ ፤ራሱን ለዉርደት፡፡

ወርሐ የካቲት በባተ ቁጥር በአገራችን ታሪክ ላይ የራሳቸዉን አሻራ አስቀርተዉ ያለፉትን ግዙፋን ክስተቶች መዘከር የተለመደ ነዉ ። ጀግኖች አያት ቅድመ አያቶቻችን በዳግማዊ አጼ ምኒልክ አዝማችነት አድዋ ላይ የተቀዳጁት ድልና ከአርባ ዓመታት በኋላ አዲስ አበባ ላይ የፋሺስቶች ፍጅት ሰለባ ሆነዉ የወደቁቱ ሰማዕታት ሁሌም ይታሰባሉ ፡፡ የአድዋዉ ድል ኢትዮጵያዉያን ለሀገራቸዉ ነጻነት ያላቸዉን ቀናዒነትና አይበገሬነት ከማሳየት የሚገዝፍ መጠነ ርዕይና አንድምታ ያለዉ ነዉ ።በአጋጣሚዉ ፤ ምዕራባዉያኑ አቅኚዎች "ያልሰለጠነ" ብለዉ ለሚያጣጥሉት አፍሪካዊ ኃይል ተንበርክከዉ የሽንፈትን ጽዋ በመጎንጨታቸዉ በሃፍረት ሲያቀረቅሩ፤ ነጻነቱንና ክብሩን የተነጠቀዉ የጥቁር ዘር ደግሞ በኩራት አንገቱን የሚያቀናበትን አብነት ተቀዳጅቷል።

በዚሁ ወር ዉስጥ በሰማዕትነታቸዉ ቀን መድበን የምንዘክራቸዉ ኢትዮጵያዉያንም ለትዉልድ አስቀርተዉት ያለፉት ተምሳሌያዊ አስተምህሮ ከአድዋዉ ድል ጋር የሚሰናኝ እንጂ፤ የሚጣረስ ከቶ አይደለም ። በዕለቱ በሀገር ፍቅር ስሜት የነደዱ ሁለት ቆራጥ ኢትዮጵያዉያን ፤አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ፤ በፋሺስቶቹ ቁንጮ በማርሻል ግራዚያኒና ባለሥልጣናቱ ላይ ቦምብ በመወርወር የወሰዱትን ርምጃ የፋሺስቶቹ የበቀል ምላሽ ተከተለዉ ። በዚህ ፤ዕድሜንና ጾታን ባልለየ የግፍ ተግባራቸዉ በሦስት ቀናት ዉስጥ በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ሠላሳ ሺህ ኢትዮጵያዉያን ተጨፍጭፈዉ ተገድለዋል ። ጥቂት የዋሃን ግፈኞቹን ትተዉ ማሳበቢያቸዉን እንደሚኮንኑት ሳይሆን ፤ የሁለቱን ጀግኖች ቆራጥ ርምጃና ያንንም ለመበቀል፤ አዲስ አበባን በደም ኩሬ የነከራት አረማዊ ጭፍጨፋ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይናፍቀዉ የነበረዉን የነጻነት ቀን ይበልጡን አቀረበዉ እንጂ አላራቀዉም።

በየካቲት የተቀጣጠለዉን የ፲፱፻፳፱ቱን የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ተከትሎ ራሱን ሥልጣን ላይ ያቆናጠጠዉን ወታደራዊ መንግሥት ፋሺስታዊ ተፈጥሮ በመገንዘብ፤ አገዛዙ እንዲቀጥል ከተፈቀደለት በመጪዎቹ ዘመናት ከዜጎች ክብርና ከአገሪቱ ህልዉና አንጻር የሚደቀነዉን አደጋ ከወዲሁ የሚያስቀር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት ዉጥን ነድፎ በኢሕአፓ መሪነት ሲታገል የተመተረዉ ትዉልድ በበኩሉ እስከዛሬ ድረስ ዕልባት ላልተደረገበት ሕዝባዊ ትግል የአዲስ ምዕራፍ መቅድም በደሙ ቀለም ጽፎ አልፏል ። የትግልና መሥዋዕትነቱ ታሪክ በዚያ አላበቃም ። ከዚያም ወዲህ የ፲፱፻፷፮ ቱን ምርጫ በተመረኮዘ ብዙ ኢትዮጵያዉያን ሕይወታቸዉንና ኑሯቸዉን ገብረዋል ። ይሁን እንጂ ዛሬም ሕዝባዊዉ ትግል ገና ከታሰበለት ግብ አልደረሰም ።ይብሱኑ ኢትዮጵያና ሕዝቧ በታሪክ አጋጣሚ እጅጉን ከሚያስከፋ ዘረኛና አምባገነናዊ ስርዓት አረንቋ ዉስጥ ተዘፍቀዋል ። ግልግሉ ገና ብዙ ዉጣ ዉረድ፤ አያሌ ሙግትና እንግልትን ከዜጎች ይጠብቃል ።

እንደሚታወቀዉ፤ ነጻነትና ክብር በሰዉ ልጅ እሳቤ ዉስጥ ከፍተኛዉን ሥፍራ የሚይዙ እጅግ ዉድ ጽንሰ ሃሳቦች ናቸዉ ።ወደነርሱ የሚደረግ ጉዞ ሁሉ ትግልን የግድ ማለቱ የማይቀር ነዉ ። ትግል ደግሞ በበኩሉ የሕይወትንና የአካልን መሥዋዕት ያስከፍላል ።ለሙብትና ለነጻነት የሚደረግ ትንቅንቅና የዜጎች ተጋድሎ ደግሞ የድል በለስ ሲቀናዉ ብቻ የሚወደስ ፤ ካልሆነ ግን የሚነቀፍ አይደለም ። ለሀገርና ለወገን በጎ ሲባል በየትዉልዱ የሚመዘገብ የጀግንነት ሥራም ሚዛን ስፍሩ እኩል የመሆኑን ያህል እኩል ሊወደስ ይገባዋል ። ጀግኖቹንና ቁርጠኛዉን ተጋድሎአቸዉን በአክብሮት መዘከር ኅብረተሰቡ በዉለታ ምላሽ የሚከፍለዉ አነስተኛ ዋጋ ነዉ ።

ዘላለማዊ ክብር ለሰማዕቶቻችን

ሕዝባዊዉ ዴሞክራሲያዊ ትግል ያቸንፋል

## ደብዳቤዎች

**የመንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎች አመጽ ወደ ረሃብ አድማ ተሸጋ (የአወልያን ት/ቤት ፈለግ ይከተሉ ይሆን?)**

ወደ የኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች

በዚህ ደብዳቤ ያሰፈርኩትን ትዝብት በጋዜጣችሁ ላይ እንድታወጡልኝ በትህትና እጠይቃለሁ።

የመንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎች አመጽ ወደ ረሃብ አድማ ተሸጋገረ እየተባለ በሰፊው እየተዘገበ ነው፡፡ ይህ ተቃውሞ የአወልያን ት/ቤት ፈለግ ይከተሉ ይሆን?

የምግብ አቅርቦትንና የትምህርትን ጥራት መጓደል በመቃወም የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎች የጀመሩት የትምህርት ማቆም አድማ አስር ቀናትን አስቆጥሯል። ይሁን እንጂ ያቀረቧቸዉ ጥያቄዎች አድማጭ ባለማግኘታቸዉ ከመጋቢት ፲፪ ቀን ፪፻፭ ዓ.ም ምሽት አንስቶ የረሃብ አድማ መጀመራቸዉን የኮሌጁ ተማሪዎች አስታዉቀዋል ።

ተማሪዎቹ ቀደም ሲል ተቃዉሟቸዉ የተስተጋባበትን ደብዳቤ መጋቢት ፬ ቀን ፪፻፭ ዓ.ም ለፓትሪያርኩ ጽ/ቤትአስገብተዋል ። ይሁን እንጂ ለደብዳቤአቸዉ ምላሽ ካለማግኘታቸዉም በላይ ፓትሪያርኩ ዘንድ በአካል ተገኝተዉ ለማነጋገር ያደረጉት ጥረት ሳይሳካ ቀርቷል ። የኮሌጁ አስተዳደርም ተማሪዎቹ ላነሷቸዉ ችግሮች ዕልባት በመፈለግ ፋንታ የትምህርት ቤቱን ንብረት አስረክበዉ ግቢዉን ለቅቀዉ እንዲወጡ ትዕዛዝ አስተላልፏል ።

ከተማሪዎቹ ህብረት አባላት አንዱ በአሜሪካ ድምጽ ሬድዮ ፤ የረሃብ አድማ መጀመራቸዉን ገልጸ "እዚሁ ሞተን ፤ሬሣችን ነዉ ከዚህ ግቢ የሚወጣዉ የሚል አቋም ነዉ ያለን፤" ሲል ተደምጧል ።

**ከታዛቢ**

ጥሩ ታዝበዋል፡፡ የኛም ጥያቄ ይህ ተቃውሞ ወዴት ያመራ ይሆን የሚለው ነው፡፡

**ከኢትዮ ጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች**

**ከገጽ 7 የዞረ (ዜና ከተባለ)**

- የሳውዲ አረብያ ዘረኛነትና ጸረ ኢትዮጵያነት እንዳለ ሆኖ ወያኔ አሁንም በቤት ሰራተኛ ሽፋን ብዙ ሺ ወጣት ሴቶችን ለዘመናዊ ባርነት ወደ ሳውዲ አረቢያና መካካለኛ ምስራቅ እያጋዘ ነው ። በሊቢያ የበረሃ እስር ቤቶች ስቃይ ከሚቀበሉ ኢትዮጵያውያን መሐል 87 ኡ ወጣት ሴቶች ናቸውም ተብሏል ። ሳውዲ አረብያን ማጋለጥና ማውገዝ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ አለ ።
- ባለፈው ሰሞን ተጋበዝን ብለው ወደ ካይሮ ያቀኑ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች እነማን ነበሩ?

በገፍና በግፍ የታሰሩ ሙስሊም ኢትዮጵያውያንና ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ ትግላችን ይፋፋም !!

የወያኔ ሰርጎ ገቦችንና ከፋፋዮችን ከመሀላችን በነቂስ አውጥተን የሕዝብን ጎራ እናጽዳ!!

**ድርጅትዎን በፍኖተ ህብረት የኢሕአፓ ድምፅ ያስተዋዉቁ!**

ፍኖተ ህብረት የኢሕአፓ ድምፅ

በየሳምንቱ ቅዳሜ ከ2 እስከ 3 PM

በ730am ላይ በዲሲና አካባቢዉ

የሚተላለፍ ሬዲዮ ነዉ፡፡

## ዜና ከተባለ

### "ሊወጋ የመጣ ጌታዬ ቢሉት አይመለስም "
### --የኢትዮጵያ ምሳሌ

ወያኔ ኢሕአዴግ በሚለው ጭምብል አማካይነት በቅርቡ ጠቅላላ ጉባዔ ላደርግ ነኝ ብሎ ደፋ ቀና ሲል ክርሞ የጎረና ወጡን አዲስ አስመስሎ በየድርጅቱ አቅርቧል ። ለዚሁ የአረመኔዎች የባሕርዳር ድግስ ዋና አዘጋጅ ተብሎ ከዚህ በፊት ተገልሎ የነበረው ሴኩቱሬ ጌታቸው ብዙ ሚሊዮን ብር ተሰጥቶት ወደ ስራ ተመልሷል ። ባሕር ዳር ሆቴሎች በቅድሚያ ተይዘዋል--የአንዱ ትልቅ/ ሆቴል ባለቤት ራሱ አዲሱ ለገሰ መሆኑ አይዘንጋ ። ሊደለሉ የሚገባቸው ካድሬዎችም ቀደም ብለው መጥተው እንዲዝናኑ ቦታ ተይዞላቸዋል ። ወዘተ ወዘተ... ከዚሁ ጉባኤ የሚጠበቅ እምብዛም አዲስ ነገር የለም ማለት ስህተት አይሆንም ። ከወያኔ ፖሊት ቢሮ ተብዬ አባዲ ዘሞና የብሄራዊ ጸጥታ ካውንስል ሊቀመንበር የነበረው ጸጋዬ በርሔ ተወግደው በመስሎቻቸው በዓለም ገብረዋህድና ገብረመስቀል ታረቀ ተተክተዋል ። እነ ኪሮስ ቢተውም ብቅ ብለዋል። እቴጌ ሙስና በፖሊት ቢሮ ኣባልነት ስትቀጥል የወያኔ ሊቀመንበር ሚስት የሆነችው ትርፋ ኪዳነ ማርያምም እንደ አዜብና ባሏ አባይ ወልዱ የፖሊት ቢሮ አባል ተብላለች ። የወያኔ ማዕከላዊ ምርጫ ውስጣዊ ችግሮችን የሚፈታ ሳይሆን የሚያመረቅዝ መሆኑ ይታያል ። የተከፋፈለው ቡድን ባለበት ተፋጦ አለ ። የስዩም መስፍን ፤ አርከበ ዕቁባይና ብርሀኔ ገብረ ክርስቶስ ሳይወዱ ጡረታ መውጣትም የሚጠቆምና አነጋጋሪ ነው ። አፋኞቹ ጌታቸው አሰፋና ኢሳያስ ወልደ ጊዮርጊስ አሁንም በኮሚቴው ተሰይመዋል ።የሌሎቹ--ደቡብ/ብአዴን/ ኦሕዴድ/ ይዘትም ለውጥ የለውም--እነ ኩማ ደመቅሳና የሚደለሉ ሌሎች "ወጣት" ተብዬዎች በ ማኮ ገብተዋል--ግን እንኳን ኮሚቴዎቹ አመራሮቹም ዋጋና ክብደት የላቸውምና ክቁም ነገር አይቆጠሩም ። የባሕር ዳሩም ቢሆን ከባድ ለውጥ ሊያመጣ አይጠበቅም ሲሉ ታዛቢዎች ያረጋግጣሉ...

ታሪካዊው የካቲት 1966 39 ዓመትን አስቆጠረ ። አልደገመም ብሎ ማለት የግድ ይሆናል ። ብዙዎቹ ሁኔታዎች ተሟልተዋል ዛሬ እንደ ትላንቱ የካቲት ። የገዢዎቹ ቀውስ ተባብሶ ባለፈው ሁኔታ/መንገድ ሊገዙ ከማይችሉበት ደረጃ ደርሰዋል ። የሕዝብ ምሬት ሰማይ ሰማያት ደርሶ ይገኛል ። በተጨማሪ በየቦታው ተቃውሞ ፈንድቷል ። ሰላማዊም በብረትም ። ቅድመ አብዮት ሁነታ ይሸተታል ። በብዙ መቶ ሺዎች በሙስሊም ዜጎች የሚደረገውን ሰላማዊ ሰልፍ ያጤኗል ። ታዲያ የካቲት 66ን ለመድገም ምን ጎደለ ቢባል ተቃውሞው ሰፊው ሕዝብ ወይም ሁሉም ወሳኝ የሕብረተሰብ ክፍሎች ያቀፈ አልመሆኑና ተቃዋሚ ድርጅቶችም ትግሎችን ሊያቀነባብሩ አለመቻላቸውን በቅድሚያ ማንሳት ይኖርብናል:: በየካቲት 66 ትግል በትግል፤ ተቃውሞ በተቃውሞ እየታጀበ--ምንም እንኳን የሕዝብ ድል በመጨረሻ በመኮንኖች ቢቀማም--ስርዓቱን ንዶ ጥሎታል ። ዛሬ ወያኔ ተሰርስሮ ተሸርሽሮ አለ--ግን በተባበረ ትግል እየተገፋ እየተዋከበ አይደለም ። በ66 የታከሲ ነጂዎችን ተቃውሞ አስተማሪዎች፤ተማሪዎች ወዘተ ደግፈው አፋፍመውት ለገዢዎቹ ገሀነም አድርገውታል ።

ዛሬ የሙስሊም ዜጎችን ትግል አስተማሪዎችም ሆኑ ተማሪዎች ወዘተ ሲያጅቡ አልታዩም ። ወያኔ የሀገርን መሬት ለሱዳን ሲሰጥ፤ ዋልድባን ሲደፍር፤ በቤተክህነት ጉዳይም ጣልቃ ገብቶ ሲፈነጭ፤ ሕዝብን በቻይናና ሌሎችም ሲያዋርድና ሲያስበዘብዝ የሚጠበቀው ተቃውሞ አልታየም። ለዚህ ድክመት ሰበቦች ቢደረደሩም ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ እያሰኘብን ነው ። በተፋፋመና በጋራ ትግል የወያኔ ዕብሪት የፈነዳ ፊኛ መሆኑን/ እንደሚሆን ማመን ያስፈልጋልም ተብሏል ።

የወያኔው ዋና አለቃ በመሞቱና የዚሁ አምባገነን መጫወቻ በቦታው በመሰየሙ አውቅን ነቃን ያሉት ጭምር አዲስ ቀን መጣ ሊሉንና የወያኔውንም ቅጥረኛ ሊመክሩም የከጀሉ ነበሩ ። ሳይውል ሳያድር አፍረዋልና ስማቸውን መጥቀሱ አስፈላጊ አይደለም። ። ስርዓቱ ቢቃወስም አልተቀየረም፤ አልወደቀም--በሕዝብ ትግል እስኪገፋ ድረስ ማለት ነው ።ብመሆኑም የወያኔ አገዛዝ በዋና መልኩ እንዳለ አለ። ይጠራናል ብለው የቋመጡትን ሊጠራ ቀርቶ ሰጥ ለጥ ብለው እዚያው በሀገር ቤት የሚገዙለትንም ወግዱ ብሏል ። ለምሳሌ መረራ ጉዲና ብዙ ምክንያቶችን ደርድሮ በመጪው ምርጫ ድርጅቱ እንደማይሳተፍ ገልጧል ።የርስ በርስ ሹኩቻቸው በመፋፋሙ ብአዴን ተብየው ጉድ በሀገርም በውጭም ሆዳም ምሁሮች የሚላቸውን በገንዝብና በስልጣን ፍርፋሪ ማባበል ጀምሯል ። በአዳማ/ናዝሬት/ በተደረገው የኦሕዴድ ስብሰባም ካድሬዎቹ ዓለማየሁ አቶምሳን ሲያፋጥጡ ቆይተዋል። አለማየሁ ለምርጫ ያቀረባቸውም ዕጩዎች ሆኑ ባለስልጣኖች (ፍቃዱ ሰቦቃ፤በክሪ ሻሊ ወዘተም) አወዛጋቢ ነበሩ ። የበኒሻንጉል አፈ ጉባኤ ተባሮ የአንድ ቢሮ ሀላፊ ሲሆን የፌደራሉ ጸረ ሙስና ምክትል ኮሚሽነር ደግሞ ወደ መምሪያ ሀላፊነት ወርዶ ቦታው ለወላይታው ዋዶ አዶ ተሰጥቷል ። ሹም ሽሩ ደርቷል ማለት የሚቻል ነው ።የሚገርም ባይሆንም ትግሬው አባ ማትያስም ሲኖዱ በሞላ ባልተስማማበት አቡን ተብለው በወያኔያዊ ምርጫ ተሹመዋል ።ከወደ ባዕድ ሀገርም ገብተው እነሆ መጣነ ሊሉ የከጀሉትም አፍረዋል ማለት ይቻላል ። አዬ አቡነ ጴጥሮስ! ለእምነቱ ሟች ጀግና ከወዴት ተገኝቶ!!

ወያኔ ዝርፊያውን በመቀጠል ከግል ባንኮች 15 ቢሊዮን የቦንድ ገንዘብ በብድር መልክ ከመውሰዱ ሌላ ጨምሩልኝ ሲያመጣ የግል ባንኮት በመቃወማቸው የአዋሽ ባንክ ፕሬዚዳንት ጸሐይ ሺፈራው በመኪና ሰው ገጭተሀል ተብሎ ለቀናት ዘብጢያ ወርዷል። (ከዚህ በፊት በመኪና ግጭት ክስ የታሰረው ቴዲ አፍሮ ነው) ። አይን ያለው ይይ ነው ጉዳዩ ። በነገራችን ላይ ይህ ብድር የወያኔ ባንኮችን (ውጋገን፤ አንበሳ ወዘተ) አይመለከትም ። ጦሩን ለመደለል ሲባል ለተደረገው በዓል ከቢሊዮን ብር በላይ ወጥቷልም ተብሏል ። ጦሩን ከአክራሪዋ ቃታር ጋር ለማወዳጀት ሳሞራ ዩኒስ በእጅ ተብሎ በመሯሯጥ ላይ መሆኑም ታውቋል ። ለምክር ወደ ሀገር ከተጠሩት 67 አምባሳደሮች 38 ሲመለሱ 18 ታግደዋል። የወያኔ መዋቅር "እንዳንበላ" በሚል ማስጠንቀቂያና ልመና ተገጣጥሞ መቀጠሉ የሚጠበቅ ቢሆንም ብርሌ ከነቃ ዓይነት ሁኔታ ላይ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

## ምን ይሰማ ......አገር?



-"ዋሽንግተን አይደለም፤ መንግሥተ ሰማያት ይኑሩ፤ እኔ ምንም የሚያገባኝ ነገር የለም ። ግን (አስሬ ) አመጣዎታለሁ፤ እንዲያዉቁት።"

(የወያኔዉ የቦሌ ክ/ከተማ ፖሊስ አዛዥ ሳጂን ዘመድኩን ፤ ለጋዜጠኛ ሰለሞን ክፍሌ ጥያቄዎች በምላሽ የሰጠዉ ማስፈራሪያ፤ የአሜሪካ ድምጽ ሬድዮ የካቲት ፲፬ ቀን ፪፻፭ ዓ.ም እንዳስደመጠዉ )

*ሳጂን ነፍሴ ፤ ለመሆኑ ይሔ መንግሥተ ሰማያት የሚባል ሠፈር አድራሻዉ የት ይመስልሃል፤... ከኤድና ሞል ቀጥሎ ያለ መሸታ ቤት ??*

//

"በከማል ገልቹ የሚመራዉ የኦነግ አንጃ ተመናመነ።"

(ኢትዮጲያን ሪቪዉ ድረ ገጽ ፤ የካቲት ፲፱ ቀን ፪፻፭ ዓ.ም በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዳስነበበዉ )

*ከወደ መረብ ወንዝ ማዶ የምስራች ለመስማት የጠበቃችሁ....ምን አላችሁ?/*

//

"ጁነዲን ሣዶ በኬንያ ጥገኝነት ጠየቁ፤"

(ዘሐበሻ ድረ ገጽ በየካቲት ዕትሙ ከኢትዮ ቻናል ገልብጦ እንዳስነበበዉ )

• *"አልሸሹም ዞር አሉ፤" ማለት ይህንን ነዉ ። ወትሮስ ግማሽ አካሉን ቃልቲ ጥሎ የወጣ ሰዉ ምን ርቆ መሄጃ አለዉ ?*

//

-"የህወሓት ፍጥጫ ቀጥሏል፡"

(እየሩሳሌም አርአያ የካቲት ፳ ቀን ፪፻፭ ዓ.ም በኢትዮ ሚዲያ ድረ ገጽ ያስነበቡት ዜና )

• *ወያኔ ለወያኔ ቢራገጥ ጥርስ እንደማይሳበር ደጋግመን አይተነዋል ።ዉድ ጋዜጠኛ፤ እንደዚያ ሲደረግ ይጻፉልንና ዜናዉን በጉጉት እናንብልዎ።*

//

-" ብጹዕ አቡነ ማቴዎስ ራሳቸዉን ከምርጫዉ አገለሉ ፤"

(የኢትዮጵያ ሚዲያ መድረክ በፓትሪያርኩ ሹመት ዋዜማ ያስነበበዉ ዜና)

• *አሯሯጩ ከሜዳ ሲወጣ ስሙ ብቻዉን በማሯሯጡ ይገፋበታል እንዴ ?*
*ወያኔ፤ አቡነ ማቴዎስ ፺፰ ድምጽ ማግኘታቸዉን የለፈፈ መስሎን ።*

ከገጽ 1 የዞረ

**ሙስሊሙ በናዝሬት/አዳማና በሻሸመኔ ተቃውሞውን አስተጋባ**

የአዲስ አበባ ሕዝበ ሙስሊም አልቀበል ያላቸው የወያኔ ሽመኛ መጅሊሶች ወደ ደቡብ አዋሳና ሻሸመኔ በማቅናት ድጋፍ ለማግኘት ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዲናይቱ በበለጠ ሁኔታ ከፍተኛ ተቃውሞ እንደቀረበባቸው ለማወቅ ተችሏል።

ዶ/ኪያር በተባለው አዲሱ የወያኔ ተላላኪ ሹመኛ የተመራው መጅሊስ ሕዝበ ሙስሊሙን በገንዘብ እና በጥቅማ ጥቅሞች ለማማለል በሻሸመኔ ከተማ ለ7 ቀን ፕሮግራም ይዞ የነበረ ቢሆንም ሙስሊሙ በወሰደው ቆራጥ አቋም በአንድ ቀን ብቻ ሊቋረጥ የቻለ ሲሆን ዓርብ መጋቢት 6 ቀን 2005 ዓ.ም. በሻሸመኔ አረዳ መስጊድ በተደረገ ተቃውሞ ይታሰሩት የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባሎች በአስቸኳይ ይፈቱ ተመረጡ የተባሉ አዲሶቹ አመራሮች አይወክሉንም አህባሽ የተባለው የወያኔ ፖለቲካ ነው ጥያቄያችን በሰላማዊ መንገድ ይመለስ ሲሉ ተቃውሞ ማሰማታቸው ታውቋል።

በአረዳ መስጊድ በመሰብሰብ ተቃውሞውን ያሰማ በነበረው ሕዝበ ሙስሊም ላይ የፌዴራል ፖሊስ በቦታው በመገኘት የዱላ ውርጅብኝ በማዝነብ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሱ መሆናቸው ታውቋል። ድብደባና እንግልት ከደረሰባቸው ዜጎች በተጨማሪ ከ15 ያላነሱ ወጣቶ ቀስቃሽ ናቸው ተብለው ታፍነው ወደ አልታወቅ ስፍራ መወሰዳቸውን ለመረዳት ችለናል።

በናዝሬት/አዳማ ከተማም በተመሳሳይ ሁኔታ ሕዝብ ሙስሊሙ ከሰላት ስነስርዓት በኋላ ተቃውሞ በማሰማት ላይ እንዳለ የኦሮሚያ ፈጥኖ ደራሽ እና የፌዴራል ፖሊስ በጥምረት ወደ አቡበከር መስጊድ በመግባት ከፍተኛ ድብደባ የፈጸሙ ሲሆን 12 የአዳማ ዩኒቨርስቲ ሙስሊም ተማሪዎችን አፍነው ወደ አልታወቀ ስፍራ መውሰዳቸውንም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልጿል።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የወጣት ክንፍ ድርጅት
(ኢሕአፓ ወክንድ)
**Ethiopian people's Revolutionary party Youth League**
**(EPRP YL)**

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢ.ወክንድ) ማዕከላዊ አመራር ተመሰረተ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢ. ወክንድ) ከተመሠረተ ከሐምሌ 2001 ዓ.ም. (July 2009) የኢሕአፓን አላማና ፕሮግራም መሠረት በማድረግ በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ወጣቶችን በማሰባሰብና በማደራጀት ስለ ሀገራቸው የፖለቲካ የሶሻል የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ብርቱ ጥረት ያደረገ ሲሆን ወጣቶች አገራቸውንና ወገናቸውን ለመታደግ እንዲያስችላቸው በልዩ ልዩ መንገዶች ሲያደራጅ መቆየቱ ይታወቃል። በዚህም ከፍተኛ ውጤቶችን አስገኝቷል።

የወያኔ ግፍና በደል ያንገበገባቸውና የሕዝባቸው መከራና ችግር፤ ብሶትና ብስጭት እንቅልፍ የነሳቸው ወጣቶች በስልጣን ላይ ያለውን አምባገነን ሃይል ከስልጣን አስወግዶ የሕዝባችንን አርነት እውን ለማድረግ ተደራጅቶ ከመታገል ውጭ ሌላ አማራጭ የሌለ መሆኑን በመገንዘብ በየአካባቢው ተደራጅተውና የኢሕአፓ አንድ አካል ሆነው ፓርቲው በሚያካሂደው ትግል ውስጥ በቀጥታ ተሳታፊ በመሆን ለትግሉ ከፍተኛ አስተዋጾአ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

በየአህጉሩ የተደራጁ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣት ክንፍ ድርጅት አባላት በእናት ፓርቲያቸው በኢሕአፓ ስር ተሰልፈው የኢ.ወክንድን ድርጅታዊ ይዘት ለማስፋትና ለማጠናከር እንዲሁም ትግሉን ለማቀነባበርና ለማስተባበር በዚህ በያዝነው የካቲት ወር አጋማሽ ላይ ከየአህጉሩ የኢ.ወክንድ ቅርንጫፍ የተወከሉ አባላትና እንዲሁም በአገር ውስጥ ከሚገኘው የኢ.ወክንድ አካል ተወካዮች የሚገኙበት የኢ.ወክንድ ማዕከላዊ አመራር ኮሚቴ ተመስርቷል። ይህን የአመራር አካል ለመመስረት ለወራት ዝግጅት ሲደረግበት የቆየ ሲሆን የኮሚቴው ቀዳሚ ትኩረቱ በአገር ውስጥ ብሎም በዓለም ዙሪያ የተበታተነውን ወጣት ኃይል ማሰባሰብና ድርጅቱ ውስጣዊ ጥንካሬን አግኝቶ ሕዝባዊ ትግሉ የሚፋፋምበትን መንገድ ለማጠናከር ነው።

አገሪቷን በቋንቋ ክልል ከፋፍሎ አደጋ ላይ የጣለውን፤ የወታደራዊና የጸጥታ ተቋሞችን በቁጥጥሩ ስር በማድረግ የሕዝብን መብትና ነፃነት አፍኖ ሕዝባችንን እያሰቃየ ያለውን፤ የአገሪቷን ሀብትና ንብረት እየዘረፈ መሬቷንም ለባእዳን እየቸረቸረ ባንጻሩ አብዛኛውን ሕዝብ በድህነት አረንቋ ውስጥ ከትቶ እያሰቃየ ያለውን ዘረኛውንና አምገነኑን የወያኔን ቡድን ከስልጣን አስወግዶ ለሕዝባችን መብትና ነጻነት ለማጎናጸፍ የኃላፊነቱ ድርሻ ከፍተኛ ቦታውን የሚይዘው በዛሬው ወጣት ትውልድ ላይ ነው። ሕዝባችን ባለድል ሊሆን የሚችለው ወጣቱ ትውልድ ሲደራጅና ሕዝባዊ ትግሉን አቀነባብሮና አጠናክሮ ሕዝብን ለድል ሲያበቃ ነው። ስለሆነም የሀገርና የወገን ብሶት የሚያንገበግባቸውና ለሀገራችን ለውጥ የሚሹ ወጣቶች ኢ.ወክንድን ተቀላቀለው ትግሉን እንዲያጠናክሩ ጥሪያችንን እያስተላለፍን በሌላም መንገድ ለተደራጁ ወጣቶች ትግላችንን አስተባብረን ትግሉን ወደፊት እንቀጥል የሚል መልእክት እናስተላልፋለን።

የካቲት 2005 ዓ. ም./February 2013
የኢ.ወክንድ ማዕከላዊ አመራር ኮሚቴ

ከኢ.ወክንድ የወጣ አጭር መግለጫ

በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢ.ወክንድ) ስም መግለጫ የሚያወጡና የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች መኖራቸውን የደረስንበት ሲሆን እነዚህ ግለሰቦች በማናቸውም መንገድ ኢ.ወክንድን የማይወክሉ መሆናቸውን በዚህ አጭር መግለጫ በትህትና ለማሳወቅ እንወዳለን። ከኢ.ወክንድ ጋር ለሚደረጉ ማናቸውም ግንኙነቶች በሚቀጥሉት መንገዶች መገናኘት የምትችሉ መሆናችሁን እንገልጻለን።


- ስልክ **202-291-5832**
- ኢ.ሜል- **eprpylnew@gmail.com**
- የፓስታ አድራሻ **5309 Georgia Ave. NW 2nd fl. Washington DC**
- **Website: eprpyl.com**

# ማይኔክስ



ካለፈው የቀጠለ

በክፉ ዘመን፤ ክፉ ቀን፤

መስከረም ፩ሀየ፸ ዓ.ም አዲስ ተስፋ ይዞ አልጠባም። ግድያና እስራቱ ያው የቀደመው ዓመት ቀጣይ ነበር። ብዙው ወጣት ተገድሎ፤ ከፊሉ ታስሮ፤ የተቻለው ደግሞ ተሰደደ። የተረፍነውም ብንሆን የሚጠብቀን ዕጣ የተለየ እንዳልሆነ እናውቀው ነበርና ውሎ አዳራችን ስጋት ያጠላበት ሆነ። ቁጥር ፩ የወጣት ማህበራችንን በቀበሌዎች በመነጠቃችን በዚያ በኩል ስናደርገው የቆየነው መሰባሰብና እንቅስቃሴ በሙሉ ተገታ።

ያን መሰሉ ሁኔታ በማይኔክስ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ ፈጽሞ ከእኛ የተለየ አልነበረም። ከተላመደችው ማህበር በመባረሯ ሠፈር ለሠፈር ብቻዋን ስትዞር መዋል ግድ ሆነባት። እነዚያ ሁሉ የተላመደቻቸውና የምትወዳቸው ወጣቶች ቀስ በቀስ ከአይኖቿ ሲሰወሩ በደመ ነፍስም ቢሆን መገንዘቧ አልቀረም። አልፎ አልፎ ብቅ ብለን ስታገኘን ፍንጥዝጥዝ ትልና መሬት ላይ ትንከባለላለች። ከዚያም የሱሪያችንን ጫፍ በመንከስ ወደ ቀድሞው ማህበራችን ቅጥር ግቢ እንድንገባላት ትጎትተን ነበር። እንዳጋጣሚ በዚያ ስናልፍ ከተገጣጠምን፤ ወደ ተነጠቀው ግቢያችን እንድንገባላት በምታደርገው ጥረት መግቢያው በር ላይ ከነበረው የጥበቃ ደርብ ላይ ዘልላ ለመውጣት አትቦዝንም ነበር። በዚያው በመስከረም ወር መጋመሻ ላይ በዋለው አንድ ዕለተ ቅዳሜ፤ ያን እንደመኖሪያ ቤቴ፤ እንደ ት/ቤቴና እንደ ነጻ ሜዳዬ እቆጥረው የነበረውን የማህበራችንን ቅጥር ግቢ በተሠረቀ ዕይታ ወደጎን እያስተዋልኩት አለፍኩ። እውነቱን ለመናገር በዚያ ቅጽበት አዕምሮዬ ውስጥ ሲራኮቱ በነበሩ የግል ትውስታዎቼ ሙሉ በሙሉ ተመስጬ ነበር። ወደ ገሀዱ ዓለም የመለሰችኝ ማይኔክስ ነበረች። ከእግሮቼ ሥር ድክ ድክ እያለች ትከተለኛለች። ዳቦ ገዝቼ እያበላኋት መንገዳችንን ቀጠልን።

ከመኖሪያ ቤታቸው ግቢ በመውጣት ላይ ከነበሩት፤ ከአሕመዴ እናት ጋር በድንገት ተገጣጠምን። ከቤት ከወጣ ሶስት ቀናት ስላሞላውና ስላላዩት የልጃቸውን መዳረሻ ጠየቁኝ። በዚያ የመከራ ዘመን በእናቶች ዘንድ ሁሉ የተለመደ ጥያቄ ነበርና አላስደነቀኝም። እንዳላየሁት ገልጬላቸው፤ እንዳገኘሁት ያሉኝን እንደማስተላልፍለት ቃል ገባሁላቸው። ተሰናብቼ ስለያቸው ለልጃቸው እንድሰጥላቸው ያወጡትን ገንዘብ፤ ካገኘሁት በኋላ ተመልሼ የምቀበላቸው መሆኑን ነግሬያቸው በማይኔክስ ታጅቤ ወደ አስፋልቱ ጎዳና አቀናሁ።

የሥልጤ መስጊድን በስተግራዬ ትቼ፤ ለማገኛቸው የሠፈሩ እናቶች ሁሉ ሰላምታዬን እያቀረብኩ ተረማመድኩ። ዘወትር እሸት በቆሎ ከሚሸጥበት አስፋልት ላይ እንደደረስኩ፤ ማይኔክስ እኔን መከተሏን አቁማ እንድትመለስ አደረግኩና ጎዳናውን አቋርጬ ወደማዶ ተሻገርኩ። ከአጋጣሚዎች ሁሉ የተባረከ አጋጣሚ ሆነና ብዙም ሳልርቅ አሕመዴን አገኘሁት። የእናቱንም መልዕክት ነገርኩት። ከቀትር በኋላ ያለውን ጊዜ አብረን ለማሳለፍ ተስማምተን፤ ለዚህም ከ፲ ደቂቃዎች በኋላ (፯ ሰዓት ላይ) ለመገናኘት ቀጠሮ ያዝን። እስከዚያው፤ አሕመዴ የናፈቁትን እናቱን አይቶና አረጋግቶ ለመመለስ በማቀዱ ኮረኮንቹን መንገድ ተከትሎ እየተጣደፈ አዘቀዘቀ። እኔም በበኩሌ አንድ ቦታ በመቆም የጥርጣሬ ዒላማ ላለመሆን ስል ትንሽ ፈንጠር ብሎ ወደሚገኘው የአጂፕ ጋዝ ማደያ በዝግታ መራመድ ጀመርኩ።

# ትላንትና

አሕመዴ ከአራት ቀናት በኋላ በዕለተ ሐሙስ አዲስ አበባን ለቅቆ በመውጣት ለቀጣዩ የትጥቅ ትግል ወደ አሲምባ የሚጓዝ መሆኑን በመስማቴ የቀጠሯችን ሰዓት ደርሶ እስካገኘው ቸኩያለሁ። እናም በርቀት ቆሜ ዐይኖቼን ወደሚመጣበት አቅጣጫ በማነጣጠር በጉጉት እጠብቀው ጀመር። እነዚያ ዐይኖቼ ያሳዩኝን እውነት ግና ፈጽሞውኑ ማመን ተሳነኝ። ከ በቆሎ እሸት መሸጫ አጠገብ ከሚገኘው ከቀይ ባህር ቡናቤት ትንሽ ዘቅዘቅ ብሎ ከሚገኘውና በሠፈራችን ካሉት ግቢዎች ሁሉ ትልቅ ከሆነው የነእማማ ማበዜ ግቢ አጠገብ አንድ ሰው ወድቋል።

እውነቱን ለመናገር ማንነቱን የለየሁት በማይኔክስ ጩኸትና እብደት ቀረሽ ሁኔታ ነበር። ለሰው ልጅ የመጀመሪያው ለማዳና ታማኝ ጓደኛ በመሆኑ የሚታወቀው እንስሳ አቅል ያለው ፍጡር ከሆነ፤ ማይኔክስ በዚያ ቅፅበት አቅሏን ስታው ነበር። ልብን በሃዘን ቀስፎ በሚያስቀር ሁኔታ ትጮሃለች። እኔምእንደርሷው መጮህ ጀመርኩ። በአንዲት ቅጽበት የሠራ አካሉ በሰው በላ ፋሺስቶች ጥይት ፤ ቁመናው የተለሰነበት ሥጋው ተከትፎ ከእነማማ ማበዜ ግቢ ደጃፍ የተዘራው ያ ሰው፤ ውዱና በሳሉ ጓድ አሕመዴ ነበር።

ደግሜ ደጋግሜ ጮህኩኝ። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት በአካል የተለዩትንና ተመልሶ መምጣቱን በናፍቆት የሚጠባበቁትን ህያው ወንድምና የትግል ጓድ በሞት ጠውልጎ ማግኘትን የመሰለ አስደንጋጭ ነገር ከቶ ሊኖር አይችልም። ቀልቤን እንደገዛሁ ማይኔክስን በዐይኖቼ ፈለግኳት። አንድ ፔጆ ፬የ፬ መኪና አሳድዳ መድረስ አቅቷት እያለከለከች ስትመለስ አየኋት። መኪናዋ የነፍሰ ገዳዩ አንጃ የነኤልያስ ፀጋዬ፤ የደርግ መርማሪዎቹ የነካሣሁንና የነፍቅሬ ነበረች። አሕመዴንም የገደሉት እነርሱው ነበሩ። እንድትቀመጥ አዘዝኳት። አላደረገችውም። ይልቁኑ ፤ እንደ አንበሳ እየተንጎማለለች አስከሬኑን ትዞረው ጀመር። ቀጥላም አስከሬኑ ላይ ተንከባለለችበት። የምትይዘውና የምትለቀው እስኪጠፋት በሃዘን የተመታች ሰብዐዊ ፍጡር መስላ ታየችኝ። ተኩስ የሰሙ እናቶች ብቅ ብቅ ማለት እንደጀመሩ ወደታች ወረድኩና የአሕመዴን እናት አገኘኋቸው። "ማነው የወደቀው፤ ልጄ ነው አይደል ?" አሉኝ። ልደብቃቸው አልቻልኩም፤ " አዎ ፤ አሕመዴ ነው፤" አልኳቸው በተሠበረ ድምጽ። በድንጋጤ አንዳች ነገር ያገኛቸዋል በሚል ክፉ ሥጋት ገብቶኝ ነበር።

"ታድያ ምን ያርበተበትሀል?! በትግል ወቅት መውደቅ ያለ ነው ስትል አልነበረም ?"

መልሳቸው አስደነቀኝ። የአገሬ እናቶች ዕጣ ሁሌም ብርቱ ፈተና የተመላው መሆኑን አሳምሬ አውቃለሁ። ይሁን እንጂ፤ በዚያ የፍጅት የግድያ ዘመን፤ ልጇን በግፍ የተነጠቀችበትን ክፉ አጋጣሚ በጽናት ፈርጥማ የተቀበለች እናት ስንቷ ትሆን ?/...የአሕመዴ እናት ያሳደሩብኝን አድናቆት ሳላገባድደው እህቱ ፋጤ ደረሰች። ከርሷው ጋር ተያይዘን ወደ አስከሬኑ ሮጥን። በሥፍራው ማንም አልነበረም። ሁሉም ሰው በፍርሃት ተውጦ በርቀት ሆኖ ነበር ወደዚያ የሚያንጋጥጠው። ማይኔክስ ብቻዋን ሬሣውን በአደራ ስትጠብቅ አገኘናት። ከነማበዜ ግቢ በአንዲት ሴት (ምናልባትም በራሳቸው )ተደርጎ ሊሆን ይችላል፤ አስከሬኑ ድሪያ ለብሶ ጠበቀን። እኔ ከራስጌ፤ ፋጤ ደግሞ ከግርጌ ሆና በመያዝ የአሕመዴን ሬሣ ተሸከመን፤ "ለዘመናት"ን እየዘመርን ወደ ቤት ጉዞ ጀመርን።

መድረሳ (የቁርዓን ት/ቤት ) ውስጥ በመማር ላይ የነበሩ ታዳጊ ወጣቶች አስከሬኑን እንዲያጅቡ በዑዝታዙ (በመምሕሩ) ታዝዘው ኖሮ ወዲያውኑ እየተንጋጉ ተከተሉን። በሚኮላተፍ ግን በሚጣፍጥ አንደበታቸውም፤ አዜሙለት።

"ቢወቀጥ አጥንቴ ....ቢንቆረቆር ደሜ፤<br>ለአዲስ ሥርዓት ልምላሜ፤<br>ፍጹም ነው ዕምነቴ .....የትግሉ ነው ሕይወቴ፤".......

አስከሬኑን ተሸክመን ከተወረሰው የማህበራችን ግቢ ፊት ለፊት፤ "ለዘመናት"ን ባንሠራራ ስሜት፤ ሲቃ በተጫነው ድምጽ ዘመርነው። በዚያ አጋጣሚ፤ ከእኛ በተለየ መልኩ ከማህበሩ ጠባቂ ላይ ካልተከመርኩ በሚል ለገላጋይ ያስቸገረችው ማይኔክስ ብቻ ነበረች። ሁኔታችን ያላማራቸው በዕድሜ የተለቁ አባቶች አስከሬኑን ወደቤት እንድናስገባው አዘዙን። እንደተባልነው አደረግን። እናም ሬሣው በእስላማዊ ሥርዓት ይገነዝ ጀመር። በዚህ ጊዜ የአሕመዴ እናት ወደ ቤቱ በስተኋላ ወስደውኝ የተቀባባሁትን ደም ከላዬ አጠቡልኝ። ከዚያም፤ የጓሮውን መውጫ በር ስለከፈቱልኝ ሾልኬ ወጣሁ። ሌላ ምርጫ አልነበረኝም ። በመቀጠል፤ ለቀስተኛው ተሰባስቦ ጉዞውን ወደ እስላም መቃብር አደረገ። ወደ ሠፈሬ አቀናሁ። በአሕመዴ ቀብር ላይ መገኘት እንደማልችል ግልጽ ነበር። በርቀት ሆኜ፤ በሐዘን ተቆራምጄ ከተቀመጥኩበት አለት ደንጊያ ላይ እንዳለሁ፤ ጓዴን በለሆሳስ ቃል ኪዳን ወደ ዘለዓለማዊው ቤቱ ሸኘሁት፤

"የተሠዋህለት ትግል ይቀጥላል!

እናቸንፋለን/"።

አሕመዴን ከቀኑ ፯ ሰዓት ላይ የገደለው የፋሺስት ቡድን ቀጥሎ ሞርጌጅ ባንክ ሥራ የጀመረውን፤ የማህበራችንን አንጋፋ ጓድ መንግሥቱ ጥላሁንን ከቤት ወጥቶ ሰንጋ ተራ መስቀለኛው መንገድ ላይ ታክሲ ሲሳፈር አገኝተው በጥይት ደብድበው ገደሉት። አዲሱ መርዶ በቀዳሚው ላይ በመደረቡ ነው መሰለኝ፤ ለመቋቋም ከምችለው በላይ ሆነብኝ። በግማሽ ሰዓት ውስጥ ሁለት ምትክ አልባ ጓዶቼን አጣሁ። ከአንድ ቀን በፊት፤ በመጀመሪያ ወር ደሞዙ ለወላጅ እናቱ አልጋና ፍራሽ ገዝቶላቸው ነበር። ሆኖም የመኖሪያ ቤታቸው በር ጠባብ በመሆኑ የተነሳ በሩን ነቅሎ ለማስገባት እንድረዳው በጠየቀኝ መሠረት ከቀትር በኋላ ልንገናኝ ቀጠሮ ነበረን። የጓድ መንግሥቱ ጥላሁንን አስከሬን አስጥለን ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አመጣነው። በማግስቱ በዋለው እሁድ ማለዳ ተክለ ኃይማኖት ቤተ ክርስትያን ቀበርነው። የአሕመዴ ሥርዓተ ቀብር ከተፈጸመ በኋላ፤ በዚያው ዕለት ታላቅ ወንድሙ ተያዘ። የታናሽ ወንድሙን ሬሣ በማሸሽ ተወንጅሎ ደርግ ጽ/ቤት ታስሮ ከሰነበተ በኋላ የኢ.ት. ብር ፫፻ መቀጮ ከፍሎ መፈታቱ ተሰማ። ከአንድ ወር በኋላ ተራው ለኔ ደረሰና ተይዤ ታሠርኩ። በታሰርኩ በሣምንቱ ማይኔክስን የሚመለከት አንድ ዜና ካለሁበት ቦታ ደረሰኝ። በውድቅት ሌሊት ብቻዋን በመዘዋወር ላይ ሳለች ኢጋጨውና አራርሳ የሚባሉ ሁለት አብዮት ጥበቃዎች አንድ እስረኛ ሲነዱ ያጋጥማታል። ከመቅጽበት ዘልላ በአንደኛው የጥበቃ አባል ላይ ከተከመረችበት በኋላ ነክሳ አልለቀው ትላለች። በዚህ ጊዜ ሁለተኛው ታጣቂ፤ "ይህቺ የአናርኪስት ውሻ " በማለት ጌቶቹ በፍርሀት ለሚርዱለት ድርጅት (ኢሕአፓ) ማራከሻ በሰጡት ስያሜ ሰደባት። እናም ያቀባበለውን የዲሞትፎር ጠመንጃ አፈሙዝ ጆሮዋ ላይ አስጠግቶ መተኮሻ ምላጩን ሳበው። የስንብቷና የጣዕር ጩኸቷ ድምጽ፤ ለአንዲት ቅጽበትም ቢሆን የውድቅት ሌቱን ጸጥታ አናጋው። ማይኔክስ፤ ለተሰለፉበት ታላቅ ዓላማና ራዕይ ሲታገሉ ለወደቁት የቁጥር ፩ ወጣት የኢሕአፓ ጀግኖች ለነበራት ፍቅር ነፍሷን የከፈለች እንስሣ ናት። በእኔና በሌሎች መሰሎቼ ህሊና ውስጥ ግን ለሁሌውም ሥፍራ ይዛ ትኖራለች።

**ያለው አንድ ሲኖዶስ ነው፤ ጳጳሱም አቡነ መርቆሬዎስ ናቸው::**

መስፍን ሀ/ጊዮርጊስ

ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል ሚል አባባል አለ:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ለሁለት <<ተከፈለ>> የሚለው ውሸት ሲደጋገም ጊዜ፤ አሁን፣ አሁን እውነት እየመሰለ መጣና ተከፋፈሉ የሚለውን ቃል ዘወትር እናስተጋባው ጀመር::

ሲኖዶስ ለሁለት ተከፈለ ማለት፣ የሀይማኖት አባቶቹ በቤተከረስቲያን ስርአት(በቀኖና) ወይም በእምነት(በዶግማ) ምክንያት በሀሳብ ተለያይተው ለሁለት ተከፈሉ እንደማለት ነው:: ይህ ደግሞ ሲሆን አላየንም፤ እዚህ ውጭ አገርም ሆነ አገር ቤት ያለነው ወገኖች ሂደቱን፣ የሆነውን ነገር ሁሉ ከመጀመሪያው ጀምሮ የተከታተልን ስለሆነ እውነቱን መመስከር የሚሳነን አይሆንም::

በመሰረቱ፣ እምነት ማለት ፖለቲካ ወይም ዓለማዊ ፍልስፍና ሳይሆን፤ ከእግዚ አብሔር የተሰጠ አስተምህሮ እንደመሆኑ መጠን፤ የሀይማኖቱ አባቶች ድንገት ከመሬት ተነስተው በሀሳብ የሚለያዩበት ጉዳይ አይደለም:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላለፉት ሁለት ሺ አራት መቶ ዓመታት ሀይማኖቱን ጠብቃ እንደመቆየቷ መጠን በዚህ በኩል የገጠማት ችግር የለም ወደፊትም አይኖርም::

እርግጥ ነው አንዳዴ እምነቱን ከደው የሚያፈነግጡ የሀይማኖቱ አባቶች አይታጡም:: አርዮስን፣ መቅዶንዮስን፣ አቡሊናርዮስን እና ንስጥሮስን ያጤኗል:: ዛሬም በኢትዮጵያ እንደ ሟቹ አቡነ ጳውሎስ፣ እንደነ አባ ሳሙኤል፣ አባ ማቲያስ...ወዘተ ያሉ የሀይማኖት አባቶች ተብዬዎች ሀይማኖታቸውን ከደው፤ የባዕዳንን አላማ አስፈጻሚ ከሆነው፤ ከነፍሰ ገዳዮ ወያኔ ጋር ማበራቸውን እያየን ነው::

አሁን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ የደረሰውና እየደረሰ ያለው ችግር ግን የመከፋፈል ሳይሆን፤ ወያኔ ቤተክርስቲያኗን ለማጥፋት ገና ደደቢት ሳለ የወጠነው የጥፋት ተልዕኮ ውጤት መሆኑን ጤነኛ የሆነ ሁሉ የሚገነዘበው ነው::

በመሆኑም ወያኔ፣ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረ በኋላ፤ መጀመሪያ ካፈረሳቸው ተቋማት አንዷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን እንደነበረ የሚታወቅ ነው:: በዚህም መሰረት አቡነ መርቆሬዎስን ከመንበረ ስልጣናቸው ላይ በሀይል በማስነሳት አቡነ ጳውሎስን

# ነጻ ሀሳብ

<<ጳጳስ>> ብሎ መሾሙ እውነት ነው:: ይህንን ደግሞ ቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው ታምራት ላይኔ፣ እኔ ነኝ በሀይል ከስልጣናቸው እንዲለቁ ያደረኩት ብሎ ህያው ምስክርነቱን ሰጥቷል::

አቡነ መርቆሬዎስ፣ ታምሚያለሁ መንበሩን ተረከቡኝ ባሉት መሠረት ነው አቡነ ጳውሎስ የተሾሙት የሚለው የወያኔ የተለመደ ውሸት ነው:: አቡነ መርቆሬዎስ ታምሚያለሁ መስራት አልችልም ካሉ መልሰው ለምን ይዋሻሉ? ለምንስ አገር ጥለው ይሰደዳሰሉ? መስራት አልችልም ቢሉ ኖሮ ይሄንኑ ለሲኖዶሱ አሳውቀው፤ ሲኖዶሱ ሌላ ጳጳስ ይሾም ነበር:: ሲኖዶሱ ግን መሥራት አልቻልኩም ብለዋልና አቡነ ጳውሎስን ሾምኩ አላለም:: ይልቁንም አቡነ መርቆሬዎስ ከመንበረ ሥልጣናቸው የተነሱት በህገ-ወጥ መንገድ የቤተ-ክርስቲያን ቀኖና ተጥሶ መሆኑን አሁን ድረስ አባቶቹ እየመሰከሩ ይገኛሉ::

ወያኔ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጠላት መሆኑ የታወቀ ጉዳይ ነው:: ይሄንኑም ቀደም ሲል የምናውቀው ቢሆንም ስብሀት ነጋም በተጨማሪ <<ዓላማችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርሲቲያንንና የአማራን ዘር አከርካሪ መስበር ነው>> በሚል በአንደበቱ በድጋሚ አረጋግጦልናል:: ወያኔም ምኒልክ ቤተመንግስት በገባ ማግስት በቤተክረስቲያኒቱ ላይ መዝመቱ፤ የመጣበት ዓላማ በመሆኑ እንጂ ያጋጣሚ ጉዳይ አይደለም:: አቡነ መርቆሬዎስም መጀመሪያ ኬኒያ ከዛም ወደ አሜሪካ የተሰደዱት የዚሁ የወያኔ እርኩስ አላማ ሰለባ በመሆናቸው እንጂ በመታመማቸው መስራት አልችልም ብለው አይደለም::

እዚህ ላይ ሁላችንም ማወቅ ያለብን አንድ ቁም ነገር ያለ ይመስለኛል:: ይኸውም፣ አቡነ መርቆሬዎስ የተሰደዱት፣ ከመንበረ ሰልጣናቸው በመነሳታቸው፤ <<ስልጣኔን ለምን አጣሁ>> በሚል የስልጣን ጉጉት አለመሆኑ መታወቅ አለበት:: ይልቁንም እኚህ ደካማ መንፈሳዊ ሰው ከሀገር ተደብቀው በመውጣት፤ በሰው አገር ስደተኛ ለመሆን የበቁት፤ ወያኔ በስውር ሊገላቸው በማቀዱ እንደነበረ በወቅቱ ሂደቱን ይከታተሉ የነበሩ ወገኖች ይመሰክራሉ:: አዲስ አበባም ብቻ ሳይሆን ኬኒያም ድረስ ተከትሎ ሊገላቸው ሞክሮ ነበር ይባላል- ነፍሰ ገዳዮ ወያኔ::

መቼም ወያኔ እንዲህ አይነት ወንጀል አይፈጽምም ብሎ ሙግት የሚገጥም ሰው ያለ አይመስለንም:: ስንቱን መርዝ ግቶ፣ ስንቱን አሳንቆ፣ ስንቱን ማጅራት አስመትቶ...በስውር የፈጀውና እየፈጀ ያለው ወያኔ፤ እኚህን ደካማ አቡን እዛው በግዞት በነበሩበት እንጦጦ በለመደው መንገድ ሊያስወግዳቸው አይሞክርም ማለት የዋህነት ነው:: አሁን ወያኔ እያስጨነቀው ያለው የሀይማኖት ንትርክም ጸጥ ረጭ ይል የነበረው በዚሁ የተለመደ ስልቱ ነበር:: ግን እሱ ሳይሆን ቀረና አቡኑ በወገኖቻቸውና በእግዚአብሔር ፈቃድ አገር ጥለው ለመሰደድ በቁ::

አንዳንድ ወገኖች፣ የአቡነ መርቆርዮስን ስደት ለሲኖዶሱ ሁለት ቦታ መከፈል ምክንያት ይመስል፤ የአቡኑን መሰደድ ከመቃወማቸውም በተጨማሪ እዛው መሞት ነበረባቸው የሚሉ ስግብግቦችና ባንዳዎች አሉ:: በጣም የሚገርመው እነዚህ ወገኖች አብዛኞቹ የወያኔ አጫፋሪዎች ቢሆኑም፤ ከፊሎቹ ግን ወያኔ ሲያሳድደን ሕይወታችንን ለማትረፍ የተሰደድን ነን ባዮች ናቸው:: በኛ እምነት ግን አቡኑ መሰደዳቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ መሰደድም በሳቸው አልተጀመረም እንላለን::

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ አንድ አገር በጠላት ወረራ ስር በሚወድቅበት ጊዜ፣ የዛ ሀገር የሀይማኖት አባቶች እና እናቶች ራሳቸውን ይሰውራሉ፤ ወይም ደግሞ ይሰደዳሉ፤ የሀይማኖት ቅርሦቻቸውን መጽሐፍፈቶቻቸውን፣ እንዲሁም ሌሎች ክፍተኛ ሚስጢሮቻቸውን በጠላት እጅ እንዳይወድቅ ያሸሻሉ:: በግራኝ መሐመድ፣ በዮዲት ጉዲት እና በጣሊያን ወረራ ዘመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አባቶችም ያደረጉት ይህንኑ ነበር:: ዛሬ በጣና፣ በዝዋይ፣ እና በሌሎችም ሀይቆች ላይ የሚገኙት ገዳማትና አብያተክርስቲያናት በዛን ዘመን ራሳቸውንና ቅርሶቻቸውን ከጥፋት ለማዳን የተሰወሩባቸው ደሴቶች ናቸው::

ቻይና ቲቤትን በወረረችበት ዘመን፣ የሀይማኖቱ አባቶች ቅርሦቻቸውን ይዘው ወደ ሂማሊያ ተራራ በመሄድ መሸሸጋቸውን አንዳንድ መጻሕፍት ያስረዱናል:: የሀይማኖቱ መንፈሳዊ መሪ የሆኑትም ዳላይ ላማ (Dalai Lama) አሁን ድረስ በሕንድ አገር በስደት ሆነው ቻይና አገራቸውን እንድትለቅ እየታገሉ ይገኛሉ:: እነቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ እነቅዱስ አትናቲዎስ፣ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ፣... አገራቸውን ጥለው የተሰደዱት በወንበዴዎች እጅ ላለመውደቅ ነበር::

ግራኝ መሐመድ(ቱርክ)፣ ዮዲት ጉዲት(ግብጽ) እና የጣሊያን ፋሺስቶች የዘመቱት በዋናነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን ለማጥፋት ነበር:: እነዚህ ሦስት ወገኖች የሀይማኖት ቅርሦችንና መጻሕፍትን በማውደም አብያተክርስቲያናትን በማቃጠል፤ የሀይማኖቱን ተከታዮች በመፍጀት...በታሪክ ውስጥ እጅግ ከፍተኛ የሚባል ጥፋት ፈጽመዋል:: ወያኔም ከነዚህ የውጭ ጠላቶች ጋር የሚመደብ ነው- እንደውም የባሰ! ::

ወያኔ ልክ እንደ ኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ነው:: ሰውነታችንን አመንምኖ የሚገለን ቫይረስ ወደ ሰውነታችን ሲገባ፣ ነጭ የደም ሴሎች (white blood cells) ይህንን ቫይረስ ለመግደል ተሰባስበው ይከቡታል:: በዚህን ጊዜ ቫይረሱ መልኩን ይለውጥና የሰውነታችንን መልክ ይይዛል:: የከበቡት ነጭ የደም ሴሎችም<<ይሄማ የኛው ነው>> ይሉና ሳይገሉት ይተውታል::


**ኢትዮጵያ ጋዜጣን**

*በተለያዩ ድረ ገጾች

ሀ. Eprp.com

ለ. Asimba.org

ሐ. Debteraw.com ወዘተ...

*በ Face book

ያገኙዋታል!

ከገጽ 6 የዞረ

በኋላ ግን ቫይረሱ እየበዛ ይመጣና ቀስ በቀስ የሰውነታችንን ነጭ የደም ሴሎች ያጠፋቸዋል፤ በመጨረሻም አመንምኖ ይገለናል። እነ ግራኝ መሐመድ፣ እነ ዮዲት ጉዲት እና የጣሊያን ወራሪዎች ጠላጥነታቸው በግልጽ የታወቀ ስለነበር፤ የሀይማኖቱ አባቶችና እናቶች ታሪካዊ ቅርሦቻቸውን ለማሸሽ፣ ራሳቸውን ለመሸሸግና በጊዜ ለመሰደድ እድሉን አግኝተዋል። ወያኔ ግን <<አሕአዴግ>> ብሎ ኢትዮጵያዊ መስሎ፤ በዴሞክራሲ ስም ተሸፍኖ ስለመጣ፤ ምንም እንኳ ጠላትነቱን ጥቂቶች ቢገነዘቡትም አብዛኛው ሕዝብ በመደናገሩ፤ የሀይማኖት አባቶቹም ቀድመው ራሳቸውን ከወያኔ ጥቃት ለመከላከል ሳይችሉ ቀርተዋል።

በመሆኑም ወያኔ፣ ኢትዮጵያዊ መስሎ፣ መጀመሪያ ጳጳሱን አቡነ መርቆሬዎስን በስውር ማስወገድ፤ ኢትዮጵያዊ ጳጳስ መስሎ (አቡነ ጳውሎስን በመሾም) የቤተክረስቲያኒቱን እምነት በባዕድ እምነት መለወጥ፤ የሀይማኖት ቅርሶችን መዝረፍ፤ መጽሐፍቱን ማውደም፤ ገዳማቱን ማቃጠልና እንደ ዋልድባ ያሉ ገዳማትን ደግሞ በልማት ስም ማጥፋት…ወዘተ ነበር አቅዱ በዲያቢሎስ ስልት! ትራንስፎርሜሽን እያለ የሚጠራውም ይህንኑ የጥፋት ድርጊቱን ነው።

እንግዲህ ከታሪክ እንደምንማረው፤ የትኛውም አገር በጠላት በተወረረበት ዘመን ሁሉ የሀይማኖት አባቶች ራሳቸውን መሰወራቸው ወይም አገር ጥለው መሰደዳቸው አይቀርም። አቡነ መርቆሬዎስም ስደት የገቡት አገሪቱ በጠላት እጅ በመውደቋ እንጂ ሲኖዶሱ ለሁለት በመከፈሉ አይደለም። እንደ ወያኔ ያለ ክፉ ጠላት መሀል አገር ተቀምጦ የሀይማኖት አባቶቹ በሰላም ሊቀመጡ አይችሉም። አገርቤትም ያሉት በሰላም አልተቀመጡም፡ እየተሰደዱ፣ እየተገደሉ፣ እየታሰሩ፣ ከገዳሞቻቸው እየተፈናቀሉ ነው ያሉት።

በሌላም በኩል አቡነ መርቆሬዎስ እዚህ አሜሪካን በስደት እያሉ ሲኖዶስ በማቋቋማቸው እና ሲኖዶሱ ለሁለት በመከፈሉ ግራ ተጋባን የሚሉ ወገኖች አሉ። በምንም አይነት ግረ ልንጋባ አይገባም፤ ሲኖዶሱ ያው ቀድሞ የነበረው ነው፤ ልዩነቱ መቀመጫውን አሜሪካ ማድረጉ ነው። አቡኑ ሲኖዶስ ለማቋቋም የበቁት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሕጋዊ ጳጳስ በመሆናቸው እና ሕጉ ሲለሚፈቅድላቸው እንጂ በሌላ ምክንያት አይደለም። አንድ ብቻቸውን ቢሆኑ እና ሲኖዶስ ማቋቋም ባይችሉ እንኳ፤ አገር ከጠላት ነጻ እስክትወጣ ድረስ እንጠብቃለን እንጂ፤ ማንም ወንበዴ ከመሬት ተነስቶ ሲኖዶስ አቋቁሚያለሁ ሊለን አይችልም።

ሀገር ቤት ያለው ሲኖዶስ የተቋቋመው፤ በወያኔ እና እንደ አባ ማቲያስ፣ አባ ሳሙኤል፣…ባሉ የበግ ለምድ በለበሱ የሀይማኖት አባቶች ነን ባዮች መሆኑ የተረጋገጠ ነው። እነዚህ ወገኖች ዛሬ እውነተኛ ሀይማኖት አባቶችን፣መነኮሳትን የሚሳድዱ፣ የሚያሳስሩ፣ የሚያዋርዱ፣ የሚያስገድሉ፣ ገዳማትን የሚያፈርሱ፣…ሲሆኑ፣ ትላንት ወያኔ ጫካ በነበረበት ወቅት መረጃ በማቀበል የተሰማሩ፤ እንዲሁም በቀይ ሽብር ተሳታፊ በመሆን ንጹሀንን ያስፈጁ…የሕዝብ ጠላቶች ናቸው።እነዚህ ያቋቋሙትን ሲኖዶስ እንደሲኖዶስ ቆጥሮ፤ ሲኖዶሱ ለሁለት ተከፈለ እንዴት ሊባል ይቻላል።

ወየኔ ሲኖዶስ ሊያቋቁም ይችላል፤ ማንንም ወንበዴ ከመሬት አንስቶ ጳጳስ ነው ብሎ ቢሾም ማንም ከልካይ የለውም። እንኳን ሲኖዶስ የፖለቲካ ድርጅት በመፍጠር የተካነ ነው። ይሁንና የፈለገውን ያህል ሲኖዶስ አቋቋምኩ ቢል ተከታይ አያገኝም።

እሱ ካሰማራቸው ከሀዲ አገልጋዮቹ እና ሆዳሞች በስተቀር፤ በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ ሀገር የሚገኙት ዘጠና ዘጠኝ በመቶ የሚሆኑት የሀይማኖቱ አባቶች ከአቡነ መረቆሬዎስ ጋር ናቸው። ከጥቂት አጫፋሪዎቹ በስተቀርም በሀገር ቤት የሚገኘው በሚሊዮን የሚቆጠረው ምዕመናንም ሆነ በውጭ ሀገር ያለው አቋሙ ያው ተመሳሳይ ነው። እናም የተከፋፈለ ሲኖዶስ አለ ለማለት አይቻልም።

እዚህ ላይ ሁለቱን ሲኖዶሶች እናስታርቃለን እየተባለ የሚነገረውም ነገር መነሳት ያለበት ይመስለናል። እንደ እውነቱ ከሆነ እርቅ ወይም ሽምግልና የሚባለው የሀይማኖት አባቶቹ በአንዳች ነገር ቢለያዩ እና ባይስማሙ ነበር። ቤተ-ክርስቲያኗ ላይ የደረሰው ችግር ምክንያቱ ወያኔ ሆኖ ሳለ፤ ሁለቱን ሲኖዶሶች እናስታርቃለን ማለት፣ምዕመናኑን ግራ ከማጋባት ባለፈ ወያኔ ላቋቋመው ሲኖዶስ እውቅና እንደመስጠት ይቆጠራል። እርቅ ብለው ለተነሱት የሀይማኖት አባቶች ያለን አክብሮት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከወያኔ ጋር እርቅ ማድረግ አይቻልም ብለን እናምናለን። ሀገርን፣ ሀይማኖትን ለማጥፋት ከመጣ ጠላት ጋር መታረቅ አይቻልም ። አቡነ መርቆሬዎስም ሆኑ ሌሎች አባቶች፣ እንደ በረከት ሰምኦን፣ ስብሃት ነጋ፣ አባይ ጸሐዬ፣ ደብረ ጺዮን፣…ከመሳሰሉ ነፍሰ ገዳዮች ጋር ታርቀው ሊገቡ አይችሉም።

በአቡነ መርቆሬዎስ የሚመራው ሕጋዊው ሲኖዶስ ስደት ከገባ ከሀያ ዓመታት በላይ አስቆጥሯል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሀሉ <<ሁለቱ ሲኖዶሶች የሚለው አጠራር በተለይ በሀገር ቤት የተለመደ አልነበረም። <<አባ ጳውሎስ>> ጳጳስ ሆነው በተሾሙ ማግስት ጀምሮ ይኸው ወያኔ ያቋቋመው ሲኖዶስ ከፍተኛ ተቃውሞ ነበር የገጠመው። እንደ ሊቀ ሊቃውንት አለቃ አያሌው አይነት ታላቅ መንፈሳዊ ሰው ምዕመናኑ ወደ-ቤተክርስቲያን እንዳይሄድ ባደባባይ ይገዝቱበት የነበረበት ወቅት ሲሆን፤ ምዕመናኑ ደግሞ አቡነ ጳውሎስ ላይ ድንጋይ ይወረውርና ጮክ ብሎ ያወግዛቸው የነበረበት ዘመን መሆኑ የሚታወስ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን፣ ሀገር ቤት የሚገኘውን ሲኖዶስ ወያኔ ያላቋቋመው ይመስል <<ሁለቱ ሲኖዶሶች>> እያልን ምዕመናኑን እናደናግር ጀመር።

ይህ አይነቱ አጠራር በፍጥነት መታረም አለበት እንላለን። ያለው አንድ ሲኖዶስ ነው፤ ሀገር ቤት ያለውን በወያኔ የተቋቋመው ሲኖዶስ በሚል መለየት እንችላለን። አሁን በወያኔ የተሾመውን <<ጳጳስም>> በወያኔ የተሾመው አስመሳይ ጳጳስ ብለን ከአቡነ መርቆሬዎስ መለየት አለብን። በፁዕ ወቅዱስ ብለን የምንጠራ ከሆነ ግን እኛም ከወያኔዎቹ ጋር ተደመርን ማለት ነው። ቅዱስ ሲኖዶስ የሚባለው በእግዚአብሔር ፈቃድ የተቋቋመ ው ብቻ ሲሆን፤ ብፁዕ ወቅዱስ የሚባለው ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ የተመረጠ አባት ብቻ ነው እንጂ በወያኔ ተቋቋመ ሲኖዶስ በወያኔ የተመረጠ ጳጳስ አይደለም።

በዚህ በኩል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ የሆንን ምዕመናን ሁሉ፣ ለእውነት ስንል፣ ለሀይማኖታችን፣ ላገራችን ስንል በጽናት መቆም አለብን።እዚህ እዛ መርገጥ የለብንም፤ መወላወልም አይገባንም፤ ከሀዲዎች፣ አድር ባዮችና ሆዳሞች በሚያሰራጬት ወሬ መደናገር መወናበድ ለብንም። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን ሲኖዶስ አንድ ናት፤ ጳጳሱም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መረቆሬዎስ ናቸው ብለን እንደ አንድ ሰው መቆም መቻል አለብን-አራት ነጥብ።

በመጨረሻም፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አሳድጋ፣ አስተምራ እዚህ ያደረሰቻቸው አንዳንድ መምህራን፤ <<ገለልተኛ ነን>> ይላሉ የሚል ነገር ይሰማል። ማ ላይ ቆመው ነው ገለልተኛ ነን የሚሉት? ማ ላይ ቆመሽ… የትኛው ሲኖዶስን ይዘው ነው ሕዝቡን የሚሰበስቡት? ነው ሕዝቡን ለመሰብሰብ የራሳቸው ሥልጣን አላቸው? በርግጥ እነዚህ ወገኖች ገለልተኛ ነን የሚሉ ከሆነ ሀገራቸውን፣ ሕዝባቸውን ፣ሀይማኖታቸውን ክደዋል ለእውነት መቆም ተስኗቸዋል ማለት ነው። ነገ ሀገር ነፃ ስትወጣ ከየትኛው ሲኖዶስ ጋር ሊሆኑ ነው?! እርግጠኛ ነኝ እነዚህ ወገኖች አቋማቸውን ቀይረው ከህጋዊው ሲኖዶስ ጋር እንደሚቀላቀሉ። አለበለዚያ ጨው ለራስህ ስትል…ይባለል።

ከገጽ 3 የዞረ (ዜና ከተባለ)

**እስቲ የሚከተሉትን ጊዜ ሰጥተን እንመልከታቸው፤**

- ወያኔ ወያኔነቱን በመቀጠል 28 (!) ተቃዋሚ ድርጅቶች የጋራ ስምምነት ሰነድ ሊፈራሙ አዳራሽ ሲፈልጉ አስከልክሏቸው በመኢአድ ቢሮ መፈራረም ሲገደዱ ራሱን ሰማያዊ ፓርቲ ብሎ የሚጠራው ቡድን ደግሞ ገንዘብ ለመሰብሰብ በዋቢ ሸበሌ የራት ግብዣ ተክልክሎ ቡድኑ ለኪሳራ ተዳርጓል ። ይኅው ቡድን የፋሺስት ጣሊያንን ግፍና የግራዚያኒን ሃውልት መሰራት በመቃወም ሰልፍ ሊያደርግ ሲልም ታግዶ መሪዎቹ ለአንድ ቀን ታስረዋል ## የፖለቲካ ፌንጣ የሚል ቅጽል ስም ያላቸው ዶር ያዕቆብ ሀይለማርያም ከዚሁ ሰማያዊ ፓርቲ ጋርና ዙሪያ ሀይ ሀይ ማለታቸውና ምናልባትም መሪ ሳይሆኑ የማይቀር በመሆናቸው አዲዮ ሰማያዊ የሚሉ ጥቂቶች ኣይደሉም ። ዶክተሩ በዶሮ ርቢ ስምሪት በጣም ክብረዋልም ተብለዋል ።
- በመጪው ክረምት መግቢያ ላይ ኤንጂነር ሻውል ከመኢአድ ሊቀመንበርነታቸው ይለቃሉ ስለተባለ ከወዲሁ ቦታቸውን ፍለጋ የሚሯሯጡ አሉም ተብሏል ።
- ከወደ ኤርትራ ያለው ዝምታ በጣም አነጋጋሪ ሆኖ ይገኛል ። ጦር ተብዬዎቹ የት ደረሱ? በሻዕቢያ ተይዞ ድራሹ ጠፋ ስለተባለውም ኮለኔል ታደሰ ሙሉነህ የሚጠይቅለትና የሚጮህለት ብዙም አልተገኘም ።
- ድንገት ረሳን ለሚሉና የወያኔን ጦር ኢትዮጵያዊ ይዘት ሊስጡ ለሚከጅሉ ለማስታወስ የጦሩ ኤታ ማጆር ሹም፤ የሰሜን እዝ፤ የምስራቅ እዝ፤የመከላከያ ሎጂስቲክ ሃላፊ፤ ወደ ዳርፉርና ሶማሊያ የተላከው ኡአር ሀላፊዎች፤የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ግዙፍ ተቋም ሃላፊ፤የጦሩ "ኢንዶክትሪኔሽንና ዶኩሜንቴሺን" ሃላፊ፤ የጦሮች ሀላፊ እነ ሀይለጊዮርጊስና መሀመድ ኢሳ፤ ወዘተ በሞላ የትግራይ ተወላጅ ወያኔ ጀነራሎች ናቸው! በመቶዎች የሚቆጠሩ ኮለኔሎችም እንዲሁ።
- የአሜሪካ መንግስት ጸረ ሽብርተኛ ትግል በሚል በአፍሪካ ቀንድ (በጅቡቲና ኢትዮጵያ) የጦር ሰፈሮችን መስርቶ ወታደሮችና ፓይለት ኣልባ ተዋጊ አይሮፕላኖችን (ድሮኖችን) ቢያሰፍርም የአካባቢው የጸጥታ ሁኔታ በባሰ አስጊ እየሆነ መምጣቱን ታዛቢዎች ጠቁመዋል ። የጅቡቲ ወያኔ--መሰል የፕሬዚዳንት ምርጫ የተወገዘ ከመሆኑ በላይ ትጥቅ ትግል እያካሄደ ያለው ፍሩድ የተባለውም ድርጅት እየተጠናከረ መሆኑ ታውቋል ። ሶማሊያም በአጭር ጊዜ አትረጋጋም። የኬንያና ኤርትራ ሁኔታም አሳሳቢ ነው ተብሏል። ድንቀም ሰላም ጥበቃ! የሱዳኑ በሺር በ 2015 ስልጣን እለቃለሁ ቢልም ለዚያ ጊዜም ከደረሰ ዕድለኛ ነው ።

ወደ ገጽ 2 ዞሯል

## የአሥራት አጭር የሕይወት ታሪክ

አሥራት ባደረበት ሕመም ምክንያት ሲታከም ቆይቶ ባለፈው እሁድ መጋቢት 1 ቀን 2005 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶናል። አሥራት ከእናቱ ከወ/ሮ ካሰች አየለና ከአባቱ አቶ ፋንታዬ ገብረ መድኀን እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ጥቅምት 21 ቀን 1941 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ተወለደ። ዕድገቱ በአዲስ አበባ አዲስ ከተማ (መርካቶ) ከእናቱ ጋር ሆኖ የመጀመሪያ ደረጃ ትምሕርቱን በአዲስ አባባ አርበኞች ትምሕርት ቤት ፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርቱን አዲስ ከተማ በሚገኘው የልዑል መኮንን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አጠናቋል።

አሥራት በሥራው ዓለም አዲስ አበባ ባንክ ይሠራ የነበረና የባንኩን የሠራተኞች ማኅበር ከመሠረቱት አንዱ ነበር። ማኅበሩ በሕግ ከተቋቋመም በኋላ የአዲስ አበባ ባንክ የሠራተኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት እንዲሆን ተመርጦ ለመጀመሪያ ጊዜ የባንኩን ሠራተኞች መብት ያስጠበቀውን የጋራ ድርድር በማድረግ የጋራ ስምምነት ከባንኩ ሥራ አስኪያጆች ጋር በመፈራረም የሠራተኞች መብት አስጠባቂነቱን በተግባር በወጣትነት ዕድሜው ያስመሰከረ ቆራጥ ተጋይ ነበር። የየካቲት 1966 ዓ.ም. ዓብዮት ሲፈነዳም አሥራት የሠራተኞችን መብት በመደፍጠጥ በነፃ የመደራጀትን መብት የነፈገውን የደርግ ፋሺሽታዊ መንግሥት ከኢሠአማ የትግል ጓዶቹ ጋር በመሆን አጥብቆ በመታገሉ በቀንደኝነት በቀይ ሽብር ሊመታ ይፈለግ የነበር ጀግና ነበር።

ከ1969 ዓ.ም. በኋላም ወደ ገጠር (ትግራይ አሲምባ) የኢሕአፓን ጦር ኢሕአሠን በመቀላቀል ሲታገል ከፉኛ ቆስሎ ወደ ሱዳን ለሕክምና እስከወጣበት ጊዜ ድረስ በገጠር ከደርግና ከዘረኞች ጋር ተፋልሟል። እንደ ኤውሮፓውያን አቆጣጠር በ1980ቹ ከሱዳን ወደ አሜሪካ በስደተኝነት ከመጣ በኋላ በብሉ ክሮስ ብሉ ሺልድ ኢንሹራንስ ኩባንያና በፎርድሃም ዩኒቨርሲቲ እየሠራ ከሚወዳት የትዳር ጓደኛው ወ/ሮ ታደለች ጉተማና ከልጁ መሪ ኣፋን ጋር በኒውዮርክ ብሩክሊን ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለያቸው ድረስ ኖሯል። አሥራት እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በኢሕአፓ አባልነት በጽናት የታገለ ጓድ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ሀገሩን ወዳድ፣ ሁሉን እንደጠባዩ የሚያቀርብና የሚያከብር ተወዳጅ ወንድም ነበር።

***IN LOVING MEMORY***



አሥራት አፋን

**(አሥራት ፋንታዬ ገብረ መድኅን)**

ጥቅምት **1** ቀን **1941 -** መጋቢት **1** ቀን **2005**

***ሥሙን ተገበረ አሥራት አመረረ!***

ለእጀ ሸካራውም ለእግረ ሰንጣቃ
ራስህን ሰጥተህ ሆንኸው ጠበቃ
አንት! ያንጠረኛ ወገን የመንገድ አዳሪ
አንት! ለፍትሕ ተሚጋች ቃል ኪዳን አክባሪ
የጫካው አንበሣ የከተማው ነብር
መልክህን ሳታበላሽ ቁንጅናህን ከምድር
ሥሙን ተገበረ
አሥራት አመረረ!
ደከመኝ ከማይሉት የዘለዓለም ጉዞ
ዕውነቱን ጠብቆ ቃል ኪዳኑን ይዞ
መዋጥ ቢቸግርም ልክ እንደ መተሬ
ሄዶብሻል አሥራት እሪ በይ ሀገሬ

ጓድህ ዓሊ ሁሴን

### ጓድ ፋሲካ በለጠ የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባል በጓድ አስራት አፋን ቀብር ስነ ስርዓት ላይ ያደረጉት ንግግር

ዛሬ የሕዝብ የቁርጥ ቀን ልጅ የሆነውን ወንድማችንን አጥተናል። ጓዳችን፤ ወንድማችን፤ የትግል አጋራችን፤ ጓደኛችን የሆነው ጓድ አሥራት ለአንዴም ለመጨረሻ ጊዜም ተለይቶናል። ከእኛ በመለየቱ በጣም የሚያንገበግበንና የሚያቃጥለን፤ የምንወደውና የምናከብረው ጓዳችን ጓድ አስራት ምን ዓይነት ሰው እንደነበር የምስክር ቃል ለመስጠት በቃላት ብዛትና ድርደራ ብቻ የምንወጣው አይደለም። በደፈናው አሥራት በጣም ልዩ የሆነ ታላቅ ሰው ነበር።

አስራት ገና በለጋ ወጣትነቱ የሕዝብና የሀገር ፍቅር ያንገበገበው፤ ለሀገርና ለወገን ፍቅር ሲል ኑሮውን፤ ምቾቱን፤እንዲሁም ቤተሰቡን አሳልፎ ለሕዝባዊ ትግል የሰጠ እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጅ ነው። ለሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት እንዲሁም ለአገር ብልጽግናና እድገት ሲካሄድ በነበረው ትግል ውስጥ መሳተፍ የጀመረው ቀደም ብሎ ቢሆንም አስራት የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲን የተቀላቀለው ከየካቲት 66 እንቅስቃሴ በኋላ ነው። በሠራተኛው ማህበር ውስጥ ሲያደርገው የነበረው እንቅስቃሴ በመታፈኑና በሕይወቱም ላይ አደጋ በማንዣበቡ በ1969 ዓ.ም. ወደ አሲምባ በመሄድ የኢሕአፓን ሠራዊት ኢሕአሠን ተቀላቅሎ ለሕዝብ ልእልና ለዴሞክራሲና ለአንድነት ሲካሄድ ለነበረው ትግል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። አስራት የትግል ሜዳ ውስጥ በነበረት ወቅት በርካታ የጦር ሜዳዎች ላይ ውሏል። ለሀገርና ለወገኑ ካለው ጽኑ ፍቅርና እምነት የተነሳ ረሃብን፤ ውሃ ጥማትን፤ በበረሃ፤ በተራራ በቁልቁለትና በሸለቆ ረጅም መንገድ መጓዝን፤ ብርድና ሐሩርን፤ ጎርፍና ዶፍ ዝናምን እንዲሁም ሌሎች በትግሉ ሜዳ የነበሩ እልህ አስጨራሽ ችግሮችን ተቋቁሞ ትግሉን በጽናት አካሂዷል፤ ደሙን አፍሷል፤ አጥንቱን ከስክሷል። ከጠባብ ብሔረተኛው ወያኔ ጋር በተደረገ ጦርነት ቆስሎ ለህክምና በመጀመሪያ ወደሱዳን ከዚያም ወደ አሜሪካ ሊመጣ ችሏል።

የአሜሪካ ጉዞው አስራትን በአካል ከትግል ጓዶቹ ቢለየውም ከትግሉና ከድርጅቱ ግን አልቆራረጠውም። ከድርጅቱ ጋር የነበረው ግንኙነት ለአንድ ቀንም እንኳ አልተቋረጠም፡፤ ጓድ አስራት ለህዝብ ልእልናና ለሀገር ብልጽግና ያለው እምነትና ስሜት ጥልቅና ከፍተኛ ስለነበር ለረዥም ጊዜ በኖረበት በኒውዮርክ ከተማ በሚገኘው የኢሕአፓ መዋቅር ውስጥ ግንባር ቀደም ተሳታፊ በመሆን ኢሕአፓ እያካሄደ ያለውን ትግል በማጠናከርና በማስተባበር ትግሉ ወደፊት እንዲገፉ የበኩሉን አስተዋጽኦ ከማድረግ አንድ ቀንም ወደኋላ ያለበት ጊዜ አልነበረም። ባለው አቅም፤ ባለው ችሎታ ከሚችለው በላይ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ከትግል አስተዋጽኦው ከእምነቱና ከጽናቱ በተጨማሪ ጓድ አስራት በጣም በርካታ የሚወደዱና የሚታወሱ ባህሪያት ነበሩት። በመጀመሪያ ጓድ አስራት በጣም ደግ ሰው ነው። ለሰው የሚጨነቅ፤ ለሰው ችግር ፈጥኖ የሚደርስ ነው። የሰው ችግር ስለሚከብደውና መንፈሱን ስለሚረብሸው እርሱ እንኳ ከአቅሙ በላይ ቢሆንበት እንኳ ሌሎችን በመጠይቅና በማስተባበር የሰውን ችግል ለማቃለል ዘወትር የሚጥር ሰው ነበር።
ጓድ አስራት ዝምታን ይመርጣል። ተናግሮ ሰውን የሚያስቀይምም ሰው አይደለም። ነገር ግን የማይጥመው ሁኔታ ካየ ስህተት ነው ብሎ ካመነ የልቡን ለመናገር፤ መፍትሄውን ለመጠቆም ወደኋላ የሚል ሰው አልነበረም። እከሌ ከእከሌ፤ ትንሽ ትልቅ ሳይል ረጋ ባለ አንደበቱና በሰከነ ስሜቱ ሀሳቡን ገልጾ የሚከራከር፤ ስህተቶችን የሚጠቁም፤ መፍትሄዎችን የሚያቀርብ ሳይሰልች ያመነበትን አቋም ለማሳመን የሚጥር ብርቱ ሰው ነበር።
ጓድ አስራት ከሁሉም ጋር በፍቅርና በሰላም ተሳስሮ የሚኖር ነው። ከአስራት ጋር ተጣልቼ ነበር የሚል ሰው ማግኘት ያስቸግራል። አስራት በሀሳብ ከማይሳማማው ጋር መነጋገር መወያየት የማይቸግረው ቅን ሰው ነበር።

ጓድ አስራት ተጨዋች ነበር። ጨዋታውና ቀልዱ ከጓደኞቹ አክብሮትና ፍቅር አስገኝተውለታል
የኢሕአፓ አባላት በጓዳቸው በጓድ አስራት መለየት የተሰማቸውን ስሜት የሚገልጹት በከፍተኛ ቁጭትና የሀዘን ስሜት ነው። ጓድ አስራት እድሜ ልኩን ያሳለፈበትና ከፍተኛ መስዋእትነት የከፈለለት የሕዝብ ትግል ዳር ደርሶ ሕዝባችን የመብቱ ባለቤት መሆኑን ሳያይ ህይወቱ ቢያልፍም አብረን ትግሉ በጀመርነውና በተኪው ትውልድ ትግሉ ተጠናክሮ ከዳር ሊደርስ እንደሚችል ጥርጥር የለንም። ጓድ አስራትም በህይወት ዘመኑ ለአገርና ለወገን ሲል የከፈለው መሰዋእትነት በኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ተመዝግቦ ለዘላለም እንደሚቀምጥ ምንም ጥርጥር የለንም።

ጓድ አስራት የምንወደው የምንኮራበት ወንድማችን ነው። ጓድ አስራት በህይወት ዘመኑ ያከናወነናቸው ተግባሮች ሁሉ ለሀገር ለወገን ያበረከታቸው አኩሪ ታሪኩ ነውና ባለቤቱ፤ ልጁ፤ ቤተሰብም ሆነ ቤተዘመድ እንዲሁም ጓዶቹና ወዳጆቹ መጽናናትን ያገኙ ዘንድ ምኞታችን ከፍተኛ ነው።